Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

# ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንስ ዝግጅት



**ይዘጋጁ!** የልጅዎ ትምህርት ቤት በኖቬምበር ለወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንስ ይጋብዝዎታል። ልጅዎ በትምህርት ቤት፣ በአካዳሚክ እና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ እንዴት እየሠራ(ች) እንደሆነ ለማወቅ ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ለመነጋገር ይህ ጥሩ አጋጣሚ ነው። ልጅዎ ወደሚማርበት/ወደምትማርበት ትምህርት ቤት መምጣት ሁል ጊዜ መልካም መሆኑን ያስታውሱ!

**እኛ የምናውቀው:** መምህራኖቻቸው፣ ወላጆቻቸው እና ተንከባካቢዎቻቸው ሲያግዟቸውና አብረው ሲሰሩ ተማሪዎች በጥሩ ሁኔታ ይሰራሉ። እነዚህን ስብሰባዎች እንደማስፈራሪያ ሊሰማቸው እንደሚችልም እናውቃለን። ይህ የውይይት ጥያቄ ዝርዝር ልጅዎ እንዲሳካለ(ላ)ት ለመርዳት የሚፈልጉትን መረጃ ለማግኘት ይረዳዎታል። የራስዎን ጥያቄዎችም መጨመር ይችላሉ።

**ከልጄ አስተማሪ ጋር ለመገናኘት የሚኖረኝ ዕድል ይሄ ብቻ ነው?** በትምህርት አመቱ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ከልጅዎ አስተማሪ ጋር መነጋገር ይችላሉ። የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንስ እስከሚደረግ መጠበቅ የለብዎትም። አስተርጓሚ የሚያስፈልግዎት ከሆነ ት/ቤቱ ሊያዘጋጅልዎት ይችላል።

## የልጄን መምህር ምን አይነት ጥያቄዎች መጠየቅ አለብኝ?

- ☐ ልጄ ከክፍል ጓደኞቹ(ቿ) ጋር ይስማማል/ትስማማለች?
- ☐ ልጄ ክፍል ውስጥ በውይይቶች እና በእንቅስቃሴዎች ላይ ይሳተፋል/ትሳተፋለች?
- ☐ ለንባብ እና ለሂሳብ ምን ይጠበቃል?
- ☐ የልጄን የትምህርት ጥንካሬ እና ችግሮች አንዳንድ ምሳሌዎች ሊሰጡኝ ይችላሉ?
- ☐ ልጄን ለመርዳት ትምህርት ቤቱ ምን ተጨማሪ ድጋፍ ሊሰጥ ይችላል?
- ☐ ከትምህርት ቤት ሠዓት በኋላ ልጄን የሚጠቅሙ ፕሮግራሞች፣ ክለቦች ወይም እንቅስቃሴዎች አሉ?
- ☐ ልጄን በትምህርት ቤት ሥራው(ዋ) ለመርዳት ቤት ውስጥ ምን ማድረግ እንችላለን?
- ☐ የቤት ስራዎችን ለማጠናቀቅና ለማቅረብ፣ እና ለክፍል ዝግጅት የሚጠበቁ ነገሮች ምንድን ናቸው?

## እንዲሁም የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-

- ስለልጅዎ ፍላጎቶች ለአስተማሪው(ዋ) ይግለጹ።
- ልጅዎ ማንኛውም ስሜታዊ ወይም የጤና ችግሮች ካለበ(ባ)ት ለአስተማሪው ያስረዱ።

ይቀጥላል

# ከስብሰባው በኋላ፦




### ስለ ልጄ ትምህርታዊ እድገት ይበልጥ ማወቅ የምችለው እንዴት ነው?

የኮሌጅ፣ የስራ እና የማህበረሰብ አገልግሎት ዝግጁነት መንገድ ተማሪዎች በትምህርታቸው በተለያዩ ነጥቦች ላይ እያደረጉት ስላለው እድገት መረጃ ይሰጣል። ሰነዱ በሰባት ቋንቋዎች MCPS ድረ ገጽ ላይ ይገኛል፦ https://www2.montgomeryschoolsmd.org/pathways ላይ ይገኛል።

### የልጄን ስራ በደንብ ለመከታተል ተመራጭ መንገድ ምንድነው?

"ParentVue" ይመዝገቡ። ይህ ለአጠቃቀም ቀላል የሆነ ለሞባይል ተስማሚ መተግበሪያ ነው። ለመጀመር ወይም አካውንትዎን እንደገና ለማስጀመር እዚህ ጠቅ ያድርጉ ወይም ከላይ ያለውን QR ኮድ ይጠቀሙ። ለበለጠ መረጃ ወይም የቴክኒክ ድጋፍ ለማግኘት የሚከተለውን ይጎብኙ፦ MCPS ድረገጽ > Parents > Parent Resources > ከዚያ ቀጥሎ Community Tech Support Center Information የሚለውን ጠቅ ያደርጉ።

### ልጄ የባህሪ፣ የጤና ወይም የስሜታዊነት ችግር ካለበ(ባ)ት ምን ማድረግ አለብኝ?

የልጅዎ ትምህርት ቤት ካውንስለር ከእርስዎ ጋር መሥራት ይችላል/ትችላለች። እባክዎን ለልጅዎ ካውንስለር ይደውሉ ወይም ኢሜይል ያድርጉ።

### ልጄ የቤት ስራ ለመሥራት ስለሚቸገር/ስለምትቸገር እንዴት መርዳት እንዳለብኝ አላውቅም።

ልጅዎ ከመምህሩ እርዳታ እንዲጠይቅ/እንድትጠይቅ ይንገሩ። መምህራን ከትምህርት ቤት በፊት እና በኋላ፣ እና በምሳ ሰአት ከተማሪዎች ጋር መገናኘት ይችላሉ።

ብዙ ትምህርት ቤቶች ከትምህርት በኋላ ነፃ ሂሳብ እና እንግሊዝኛ የማስጠናት እርዳታ ይሰጣሉ። ትምህርት ቤትዎ ይህን አይነት ድጋፍ የሚሰጥ ከሆነ የልጅዎን መምህር ይጠይቁ።

ወላጆች ተጨማሪ እርዳታ ሲያስፈልግ ለመምህሩ(ሯ) መደወል ወይም ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።

Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*